# የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር

## ከኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር (ኢ.ሕ.አ.ግ)
## አለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

**11/10/2006**

የኢሕአግ አርበኞች የኋላ ደጀን ሳይኖራቸውና መስዋዕትነታቸውን የሚዋደቁለት ሕዝብ በስፋት ሳያውቀው ለበርካታ አመታት ከፋሺስቱ ወያኔ ጋር ሲፋለሙ ቆይተዋል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በውጭ አገር በተለያዩ አገሮች የሚኖሩ ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊያን ግንባሩ ድረስ በመሄድ ተጋድሎአቸውን በቪድዮ ቀርጸው ለህዝብ ለማሳወቅ ከመቻሉም በላይ አስተማማኝ የኋላ ደጀን ለመፍጠር የሚያስችል የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ በማቋቋም በእንቅስቃሴ ላይ እንገኛለን፡፡

አለም አቀፍ ኮሚቴው ሲቋቋምና ገና ከጥንስሱ ጀምሮ ሕዝቡ እንዳይቀበለው ለማድረግ ብዕራቸውን የመዘዙ የወገን ጎራ ተቃዋሚዎች ቢሞክሩም እንቅስቃሴአችንን ለመግታት ቀርቶ ሊያዳክሙትም አልተቻላቸውም፡፡

በቅርቡም በፀረ ወያኔ ዘፈኖቹ የሚታወቀውና እኛም በዚሁ አቋሙ የምናከብረው አርቲስት ሰለሞን ተካልኝ ይህንን በብዙ ውጣውረድና የቁርጥ ቀን ጊዜ በቆራጥ ግለሰቦች ጥረት የተመሰረተውንና ገና በግንባታ ላይ የሚገኘውን የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ አመራር የህዝብ አመኔታ በማሳጣት ለማኮላሸት ዘመቻ መክፈቱን ስንሰማ እጅግ አዝነናል፡፡ ደጋፊዎቻችንም በዚህ የፈጠራ ወሬ ዘመቻ ግራ በመጋባት መግለጫ እንድንሰጥ በተደጋጋሚ ሲጠይቁን የቆዩ ቢሆንም እንደወገን በምንቆጥረው አርቲስት ሰለሞን ላይ መግለጫ ከመስጠት ይልቅ እንደቤተሰብ ጠብ በመቁጠር በሽማግሌዎችና በወዳጅ ዘመዶች ፊት እንደ ጨዋ ባህላችን ቁጭ ብለን በውይይት መፍታቱን ቅድሚያ በመስጠት ጊዜ ለመውሰድ ተገደን ነበር፡፡ ይሁንና በዋሽንግተን ዲሲና በአትላንታ በተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊያን በተሞከረውን ሽምግልና ለመቀበል አርቲስት ሰለሞን ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱና እንዲያውም በአፍቃሪ ወያኔ የወሬ ማሰራጫዎች ሣይቀር የማፍረስ ዘመቻውን ስለቀጠለበት ሳንወድ በግድ ለደጋፊዎቻችንና ለወገኖቻችን በሙሉ ይህንን መግለጫ ለመስጠት ተገደናል፡፡

በአርቲስት ሰለሞን ተካልኝ የሚሰራጩትን ወሬዎች በተመለከተ ሐቁ ምን እንደሆነ ዋና ዋናዎቹን ለግንዛቤ እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

1. «በውጭ አገር የተቋቋመው አለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ከአርበኛው ጋር ግንኙነትም ሆነ ውክልና የለውም» ለሚለው ክስ

   ኮሚቴው የተቋቋመው ግንባሩ በፅሁፍ የውጭ ተጠሪ ውክልና በተሰጣቸው አቶ ዘውድአለም ከበደና የግንባሩ ሊቀመንበር ኮማንደር መስከረም አታላይ በአካል በተገኙበት ከሜይ 4 እስከ ሜይ 6,2006 ዓ.ም. በጀርመን ፍራንክፈርት ከተማ በተደረገ ጉባኤ የተቋቋመ ሲሆን ከምስረታውም በኋላ በየክፍለ ሀጉራቱና በዋና ዋና ከተማዎች ኮሚቴዎችንና ቻፕተሮችን በማደራጀት የኢ.ሕ.አ.ግ.ን ዓላማና ገድል ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን አስተማማኝ መሰረት ያለው የኋላ ደጀን በመፍጠር ትብብር ለነፃነትና

ለዴሞክራሲ እንዲመሰረት ኮሚቴው ኃላፊተቱን በመወጣት ትግሉን አንድ እርምጃ ወደፊት ለማራመድ ተችሏል:: ባለፉት በጣም ጥቂት ወራት ውስጥ ይህ ኮሚቴ ያከናወናቸውን አኩሪ የስራ እንቅስቃሴዎች ከሴፕቴምበር 9 እስከ 19,2006 ዓ.ም. የኮሚቴው አመራር አባላት ወደ ግንባር በመሄድ ከግንባሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሜቴ ጋራ ስብሰባ በማድረግ የስራ ሪፖርትና ግምገማ ተደርጎ በርካታ የማጠናከሪያ እርምጃዎች ከመወሰዳቸውም በላይ የግንባሩ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሴፕቴምበር 21,2006 ዓ.ም. የጋራ መግለጫ ማውጣታቸው ይታወሳል:: ይህም የጋራ መግለጫ በድህረ ገፃችን (http://www.eppf.net/) ላይ ይገኛል::

የግንባሩን ድህረ ገፅ የሚያስተዳድረውና የሚቆጣጠረው የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይህንን የጋራ መግለጫ ከሰጠ ወደ ሌላ ዝርዝር ውስጥ ሳንገባ ክሱ መሰረተ ቢስ ስለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይመስለናል::

2. «የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ አባሎች በአርበኞች ስም ገንዘብ እየሰበሰቡ ለግንባሩ አይልኩም:: ለዚህ ማስረጃው እኔ እራሴ በጀርመን አገር ዘፍኜ ያስገኘሁት 35,000 ዩሮ አልደረሳቸውም» ለሚለው ክስ

በርግጥ የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴው በተመሰረተበት ወቅት የግንባሩነን አላማ ለህዝብ ለማስተዋወቅና የኮሚቴውን መቋቋም በይፋ ለደጋፊዎቻችን ለማብሰር ሜይ 6,2006 ዓ.ም. በፍራንክፈርት፤ ሜይ 13,2006 ዓ.ም. ደግሞ ሙኒክ ከተማ ህዝባዊ ስብሰባ ሲጠራ አርቲስት ሰለሞን ተካልኝ የሙዚቃ ትርኢት አቅርቧል::

በእነዚህ ከተሞች አርቲስት ሰለሞን ለኢሕአግ ወይንም ለትግሉ የበኩሉን አስተዋፆኦ ለማድረግ በነፃ ዘፈኑን ለህዝብ ያቀረበበት ሳይሆን እንደ ማንኛውም ሙያተኛ በሙያው እንዲዘፍን ተጠይቆ ለአውሮፕላን ትኬት፤ ለሆቴል፤ ለሙዚቃ መሳሪያ ክራይና ለሙያተኛ የተከፈለበት ዝግጅት ነው:: ከዚያም በተጨማሪ ለድምፅ ብቻ $5,000 ተከፍሎት ያቀረበው ዝግጅት ነበር:: ኮሚቴው ለዝግጅቱ ከአርቲስት ሰለሞን ጋር ሲዋዋል በ$3,000 ነበር:: በተጨማሪ ኮሚቴው ሁለተኛ ዘፋኝ አዘጋጅቶ ነበር:: ይህ ዘፋኝ በዝግጅቱ ላይ መገኘት ስላልቻለ ለሱ ሊከፈል ተወስኖ የነበረው $2,000 ለኔ ይከፈለኝ ካለበለዚያ አልዘፍንም ብሎ አዘጋጆቹም ምንም ምርጫ ስላልነበራቸው ይህንንም በተጨማሪ ከፍለውታል::

በአንፃሩ በእነዚህ ሁለት ዝግጅቶች በተደረገው ስብሰባ ከወጪቀሪ ከአዘጋጅ ኮሚቴዎች የተረከብነው ከፍራንክፈርት 1,691.31 ዩሮ ሲሆን ከሙኒክ ደግሞ 760.00 ዩሮ ነበር:: ስለዚህ በጠቅላላው ድርጅቱ ያገኘው 2,451.31 ዩሮ ብቻ ነው:: ይህ ገቢ የሸፈነው ወጪ 30% ብቻ ሲሆን ቀሪው 70% ወጪ የተሸፈነው ከሌሎች ዝግጅቶች በተገኘው ገቢ ነበር::

3. «ወደ ኢሕአግ ግንባር ጉዞ ያደረግሁት የኢሕአግን አርበኖች በመጎብኘት ለመደገፍና ሞራል ለመስጠት በራሴ አነሳሽነትና በራሴ ወጪ ደርሼ ተመልሻለሁ» በማለት በተለያዩ ሬድዮ ማሰራጫዎች ሲናገር ተሰምቷል::

አርቲስት ሰለሞን ተካልኝን የኤርትራ ጉዞ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴው ሆነ አርበኛው በከፍተኛ አድናቆት ነበር የተመለከተውና የተቀበለው:: ግን አንባቢዮቻችን እንድትገነዘቡልን የምንፈልገው አርቲስት ሰለሞን ዋነኛው ምክንያቱ ወደ አስመራ ከተማ ሊሄድ የቻለው በአስመራ ከተማ በሚደረው የአመታዊ ፌስቲቫል ላይ ለመዝፈን ነበር::

ከመሄዱ በፊት ለውጭ ጉዳይ ኮሚቴው ወደ ሰሜን እንደሚሄድ በመግለፅ እግረ መንገዱን ግንባሩን ለመጎብኘት እንደሚፈልግ አሳወቀ:: ይህንንም ስለሚያደርግ የአየር ትኬቱን ኢሕአግ እንዲሸፍንለት ጠየቀ:: ይህ ለአርበኞቹ ሞራል ተሃድሶ ይጠቅማል ከዚያም አልፎ የአይን ምስክር ይሆናል በማለት $1,847.00 የሚያወጣ ትኬት ተቆርጦ ሄዷል::

አርቲስት ሰለሞን ተካልኝ ኢዚያ ሲደርስ የግንባሩን ሞራል ከማደስ ይልቅ ስለ አለም አቀፍ ውጭ ጉዳይ ኮሚቴ የተሳሳቱና የተዛቡ ወሬዎች በመንዛት ራሱን የኢሕአግ የአለም አቀፍ ውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሊቀመንበር አድርጉኝ በማለት ሹመት እንዲሰጠው ለግንባሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ጥያቄ አቅርቦ ነበር:: የግንባሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴም ይህ ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው ገልፀውለት ነገር ግን የኢሕአግ የሚታገልበትን አላማ እስተከተለ ድረስ አባል የመሆን መብት እንዳለው ግንባሩ አስረድቶት በዛ መሰረት አርቲስት ሰለሞን የአባልነት ፎርም በሞምላትና በመፈረም የአባልነት ካርድ ወስዷል::

4. ከጥቂት ሳምንት በፊት አርቲስት ሰለሞን ተካልኝ በዋሽንግተን ዲሲ በኦክተበር 15,2006 ለኢሕአግ የገንዘብ ማሰባሰብ (ፈንድሬዚንግ) እንደ ሚያደርግ ለህዝብ በድረገፆች አስታውቆ ነበር::

ይህ ድርጊት በኢሕአግ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ ሆነም በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው ቻፕተር ፈቃድ ያልተሰጠውና እውቅና የሌለው እንደሆነና ይህም ከራሱ ከአርቲስት ሰለሞን የግል ህይወት ጋር የተያያዘ መሆኑን አገር ወዳድ ዜጎች በሙሉ እንዲረዱልን በትህትና እንጠይቃለን::

5. «ክርስትና ከሀገሬ አይበልጥብኝም ብዬ የልጄን ክርስትና ትቼው ወደ አርበኞቹ ሄጃለሁ» በማለት በተለያዩ ሬድዮ ማሰራጫዎች ሲናገር ተሰምቷል::

ሁለት የአትላንታ የኢሕአግ ቻፕተር ኮሚቴ አባሎች በተገኙበት አርቲስት ሰለሞን የልጁን ክርስት በጁላይ 16 ቀን አክብሯል::

አርቲስት ሰለሞን ተካልኝ ይህን ሁሉ የሚያደርጉት እውነት ለኢትዮጵያ አስበው ነው? በድርጅቱ አመራር ውስጥ ችግር እንኳን ቢኖር የሚፈታው በድርጅቱ የተለያዩ አካላት በሚደረግ ግምገማ እንጂ ድርጅቱን በሃሰት ቀብቶ ለጠላት ቅርበት ባላቸው የዜና ማሰራጫዎች ሳይቀር የወሬ ዘመቻ መክፈቱ ማንን ለመጥቀም ነው?

ያላደረገውን አድርጌአለሁ፤ ያልሆነውን ሆኛለሁ፤ ያልተፈጠረውን ተፈጥሯል፤ የኢሕአግ ዓላማና ግብ ለማኮላሸት ካልሆነ በስተቀር እውነቱንና ሀቁን ከእኔ ስሙ ብሎ ስብሰባ መጥራቱ እውነተኛ ታጋዮቻችን፤ ደጋፊዎቻችንና አገር ወዳድ ዜጎችን ሊያሳስት እንደማይችል ሙሉ እምነት አለን::

ከላይ በጥቂቱ ለዘረዘርናቸው በአርቲስት ሰለሞን ተካልኝ ለሚነዙ አሉባልታዎች ሁሉ በመረጃ የተደገፈ ማብራሪያ በዜና ማሰራጫዎችና በኮንፍራንስ የምናቀርብ መሆኑን በአክብሮት እናሳስባለን::

እንዲሁም ወንድማችን አርቲስት ሰለሞን ተካልኝ ይህ የጀመሩት የሃሰት አሉባልታ ዘመቻ የኢትዮጵያን የነፃነት ትግል እንደማይረዳ ተገንዝበው ወደ ትክክለኛ ስነ ምግባር እንዲመለሱ እንጠይቃለን::

ከኢ..ሕ.አ.ግ. አለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ

# አንድነት ሃይል ነው!!